# «ምርጫማ ጥሩ ነው»

መክብብ ማሞ(mekbma@yahoo.com)

የዛሬ ዓመት አካባቢ «የአንድነት ፓርቲ ወጣቶች የስነ-ግጥም ምሽት» በተደረገበት ቀን አንድ ሞገስ በመባል የሚታወቅ ደፋር ገጣሚ ከጻፋቸው ግጥሞች መካከል ስለምርጫ ይህንን አቅርቦ ነበር:-

ምርጫ እኮ ጥሩ ነው ፤ ጥሩ ነው ምርጫማ
ድምጻችን ተሰርቋል ካላላችሁማ::
ከቶ የት ይገኛል ምርጫን የመሰለ
ከውስጥም ከውጪም ታዛቢ ከሌለ::
ተቃዋሚ ፓርቲ ጠፍቶልን ካገሩ
ቢሆን ጽቡቅ ነበር ምርጫ በወሩ::
ምርጫኮ ጥሩ ነው ክብሩም የገነነ
የምርጫ አስፈጻሚው የራስ ሰው ከሆነ::
እንደ ምርጫ አስደሳች የት ይገኛል እስቲ
በተለይ ከሌለ ተቃዋሚ ፓርቲ::

ሰሞኑን ከመጪው «ምርጫ» ጋር በተያያዘ በርካታ ጩኸቶች ከያካባቢው ይሰማሉ:: አምስት ዓመት ሆነን ማለት ነው?! ትክክል ነው:: የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ «ምርጫ» የሚለው ቃል የዴሞክራቱ ፣ የኮሚኒስቱ ፣ የአልባኒስቱ ፣ የ. . .ቱ ፈሊጥ በነበረበት ወቅት «የዚህ ምርጫ ውጤት ምን ይሆን?» ብሎ ያልጠየቀ ፣ ያልተሰፈ ሰው ይኖራል ተብሎ አይገመትም:: ሆኖም ተስፋ ቀቢጽ ሲሆን ህልምም ወደ ቅዠት ሲቀየር የምርጫ አዝማቻችን የነበረው ቅንጅት «ከምንም በፊት ስምንቱ ነጥቦች ይቅደሙ» ብሎ ጠንካራ አቋም የወሰደበትን ያንን ዘመን ሁላችንም እናስታውሰዋል::

ዛሬስ? ዛሬማ ያሁሉ ቅድመ ሁኔታ ቀረና ፤ ቅንጅትም ወደ አንድነት ተቀየረና እነዚያ የዘመነኛው ፖለቲከኛ አፍ መፍቻ የነበሩ «የዴሞክራሲ ተቋማት» ፣ «ፍትሐዊ ምርጫ» ፣ «ነጻና ወገናዊ ያልሆነ የምርጫ ቦርድ» . . . የተሰኙ ቃላት ድንገት ተነኑና ሁሉም ተረሳ:: ሆኖም አንድነት ፓርቲ ሲመሰረት ከጠፉበት ፈልጎ ፣ ከተረሱበት አስታውሶ ያመጣልናል ብለን ስንጠብቅ ምሶሶና ማገር የነበረችው መሪም ጠፋችና ነጥቦቹ አንድ ትልቅ ነጥብ ሲደመር ስምንት ነጥቦች ሆነው አረፉት::

ታዲያ ይህ ሁሉ ሆኖ ፤ ወ/ት ብርቱካን ከታሰረች ፤ ከህጻን ልጇ እና አዛውንት እናቷ እንዲሁም ከደጋፊዎቿና አድናቂዎቿ ከተለየች 300 በላይ ቀናት አለፉና አሁን ትኩሳቱ ሁሉ «ምርጫ» ሆነ:: የትኩሳቱም ግለት ከፍ ከማለቱ የተነሳ ከየአካባቢው የሚሰማው ሁሉ ለሰሚ ግራ የሚያጋባ ብቻ ሳይሆን ለተናጋሪዎቹ ለራሳቸው ግልጽ መሆኑ ከማጠራጠር ደረጃ ላይ ደርሷል::

ከውዥንብሮቹ መካከል ጥቂቶቹም:-

የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ አስራት ጣሴ «አንድነት የብርቱካንን እስራት ለምርጫ 2002 ቅድመ ሁኔታ አድርጎ አያቀርብም» አሉ::
ዶ/ር ኃይሉ ደግሞ «ዋና ጸሃፊው የተናገረው የግል ሃሳቡን ነው::» በማለት አስተባበሉ::
በሌላ ዜና ደግሞ «ለተቃዋሚዎች የምርጫው መድረክ መጥበቡ ተገለጸ»::
«ኃይሉ ሻወል ፓርቲያቸው መኢአድ በመጪው ምርጫ ለመሳተፍ መዘጋጀቱን አስታወቁ»::
ፓርቲያቸው የመድረክ አባል የሆኑት ገብሩ አስራት ደግሞ «መድረክ በመጪው ምርጫ ያለመወዳደር ዓላማ እንደሌለው»ገለጹ::

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

በቅርቡ ቄለም ወለጋ ዞን ደምቢዶሎንና ባካባቢው የሚገኙ ከተሞችን የጎበኙት ሌላው የመድረክ አባል ዶ/ር ነጋሦ «በመጪው ጥቂት ወራት ሁኔታዎች ካልተለወጡ መጪው ምርጫ ነጻ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ይሆናል ብዬ አልጠብቅም» በማለት በቅርቡ ባወጡት ጽሁፍ አስታሰውቀዋል፡፡ ሌላም ፣ ሌላም፣ ብዙ ግራ የሚያጋባና እርስ በርሱ የሚጋጭ መግለጫ፡፡

*የቅንጅ ህጋዊ ወራሽ ነኝ የሚለው አንድነት ፓርቲ መድረክን ከመሠረቱ ስምንት ፓርቲዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በአጀማመሩ የቅንጅትን ስትራቴጂ እየተከተለ ያለው መድረክ በዚህ አካሄዱ ከቀጠለ በመጪው «ምርጫ» የመሳተፍ አዝማሚያ ይታይበታል፡፡ በተለይ ባለፈው 1997 ምርጫ ከተቃዋሚው ጎራ ያልነበሩ አዳዲሶቹ የመድረክ አባላት በዚህኛው «ምርጫ» ዕድላቸውን የመሞከር ፍላጎት እንዳለቸው ፍንጮች ይታያሉ፡፡ መድረክ ከተሳተፈ ደግሞ አንድነት ፓርቲም እንደአባልነቱ መሳተፉ የማይቀር ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከላይ አቶ አስራት «የብርቱካን ጉዳይ በምርጫው ለመሳተፍ ቅድመ ሁኔታ አይሆንም» ያሉት ትክክል ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዶ/ር ኃይሉ የሰጡት ማስተባበያ ተቀባይነት አይኖረውም ፤ በመሆኑም አንድነት ፓርቲ የወ/ት ብርቱካንን መፈታት በምርጫ ለመሳተፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሳያቀርብ በምርጫው ይሳተፋል ማለት ነው፡፡ ይዘገንናል!!*

*በዚህ ሁሉ የ«ምርጫ» ግርግር አንድ የተዘነጋ እውነታ መጪው «ምርጫ» የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ የተጠናቀቀ መሆኑ ነው፡፡ ሕወሃት ምርጫ 97ን ካከሸፈ በኋላ ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ ዓይነት «ስህተት» እንደማይሠራ ለተግባራዊነቱም ሥራውን ያኔውኑ መጀመሩን አብስሮን ነበር፡፡ የዚህን ጅማሬም ባለፈው ባደረገው የማሚያ «ምርጫ» «ከውጪም ከውስጥም ታዛቢ የሌለበትንና ተቃዋሚ ፓርቲ እንዳይሳተፍበት» የተደረገበት «ጽቡቅ» ምርጫ በማድረግ ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ለዓለም አሳውቋል፡፡ መጪው «ምርጫም» ከወዲሁ «የተሳካ» ለማድረግ ነሐሴ 2001 ዓም «አብዮታዊ ዴሞክራሲያውያን» ተሰብስበው በጊዜ ማሽን ወደፊት ሄደው ይሁን ወይም የምርጫ «አድቫንስ» ወስደው ብቻ እንዴት እንደሆነ ባልታወቀ መልኩ ምርጫውን ማጠናቀቃቸውንና ለአገሪቷም መሪ መምረጣቸውን አሳውቀውናል፡፡*

*ታዲያ ይህ ሁሉ እውነታ በማያሻማ መልኩ ይፋ በሆነበት ባሁኑ ጊዜ ለ«ምርጫ» እየተዘጋጁ ወይም ለመወዳደር እያኮበኮቡ ያሉት ፓርቲዎች ከመጪው «ምርጫ» ምን ይሆን የሚጠብቁት? በ1997 ምርጫ እውነተኛ ባሕርዩን ያሳየው ሕወሃት እንደሆነ አሁንም ያው ነው፡፡ ለቅንጅት ያልተመለሰ ሕወሃት ለመድረክ አይራራም፡፡ ለወ/ት ብርቱካን ምህረት ያላደረጉ «አብዮታዊ ዴሞክራሲያውያን» ለአዲሶቹ መድረካውያን ቅንጣት ታህል አይራሩም፡፡ «ያኔ በቅንጅት ጊዜ የሆነው ሁሉ ሳይታሰብበት ነው» በሚል ቁጭት ውስጥ የገባው ሕወሃት ለአሁነኛው «ምርጫ» አምስት ዓመት ሙሉ ሲያስብና ሲያቅድ ነው የከረመው፡፡ ከምርጫ ጋር በተያያዙ ለሚከሰቱ ነገሮች በሙሉ እርምጃ አወሳሰዱም እንዲሁ የተጠናበትና የታቀደ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ስለዚህ መድረክም ሆነ ሌሎች ተቃዋሚ ነን የሚሉ ፓርቲዎች በሙሉ የወ/ት ብርቱካን በእስር መቆየት የእያንዳንዳቸውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሆነ በምርጫ መሳተፍ አደጋ ላይ የጣለ መሆኑን በመግለጽ የእርሷን መፈታት ከማንኛውም ተግባር በፊት የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ አደርገው ቢያቀርቡ ጠቃሚነት ያለው ብቻ ሳይሆን ዓለምአቀፍ ትኩረትን ሊስብ የሚችል አካሄድም ነው፡፡*

*በመጨረሻም በመጪው «ምርጫ» መሳተፍ ተገቢ ነው ለምትሉ የፓርቲ አመራሮች ፣ አባላትና ደጋፊዎች አንድ ጥያቄ በማቅረብ በዚሁ ላብቃ፡- «በ1997ቱ ምርጫ ለቅንጅት ሥልጣኔን አላስረክብም ያለው ሕወሃት በአሁኑ «ምርጫ» ለመድረክም ሆነ ለሌላ ፓርቲ ይህንን መሰሉን ድርጊት የሚያደርገው ለምን ይሆን?» ስለመልሱ ሳስብ አልበርት አንስታይን ባንድ ወቅት የተናገረው ትዝ አለኝ - እንዲህ ይላል «እብደት ማለት ተመሳሳይ ነገርን ደግሞ ደጋግሞ እያደረጉ የተለየ ውጤት መጠበቅ ነው፡፡»*

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com